የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3፥16-17



«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)፥130


**Global Good News Literature**
**የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት**
**P.O.BOX 451336**
**Los Angeles, CA 90045**
email: info@globalgoodnews.org


**Copyright © 2008**




**ማውጫ**

**ክፍል ፪**


| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት ስምንት፡- መስጠት ኅብረት ........................................ | 5 |
| የመስጠት ዐይነቶች ........................................................ | 6 |
| ሀ. ዐሥራት ........................................................................ | 6 |
| ለ. መባ (በኵራት) ............................................................ | 6 |
| ሐ. የመሥዋዕትነት ስጦታ ................................................... | 6 |
| መ. ለችግረኞች መስጠት ...................................................... | 7 |
| ሠ. ለወንጌል ሥርጭት መስጠት ........................................ | 7 |
| በመስጠት ውስጥ ያለው በረከት ............................................ | 8 |
| ትምህርት ስምንት፡- መስጠት - ጥያቄዎች .................................. | 10 |

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው፡፡ «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን፡፡

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል፡፡ ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል፡፡ ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ፡፡

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል፡፡ አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው፡፡ ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን፡፡

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን፡፡





# ክፍል ፩



**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤**
**ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል፡፡»**
**መዝ. 118(119)፥130**

## ትምህርት ስምንት:- መስጠት

መስጠት ከመሰጠት (ራስን ከመስጠት) ይጀምራል:: ለእግዚአብሔር ያለንን ነገር (ጊዜአችንን፣ ገንዘባችንን፣ ችሎታችንን፣ ዕውቀታችንን፣ ...ወዘተ መስጠት የምንችለው ለእግዚአብሔር በተሰጠነው መጠን ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ያለንን ነገር እንድንሰጥ ከመጠየቁ በፊት ራሳችንን (ልባችንንና ሰውነታችንን) ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ ያሳስበናል:: «ልጄ ሆይ፣ ልብህን ስጠኝ፣ ዐይኖችህም መንገዴን ይውደዱ::» (ምሳሌ 23÷26)

«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ::» (ሮሜ 12÷1)

«ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ (የሚሰጥ) ማነው» (1ዜና. 29÷5)

## ፍቅር ካለ መስጠት አለ

እግዚአብሔር አንድያ ልጁን (ኢየሱስ ክርስቶስን) እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን (እያንዳንችንን) እንደ ወደደ (ዮሐ 3÷16)፣ እኛም እግዚአብሔርን ከወደድን ራሳችንንና ያለንን ሁሉ ለእርሱና ለወንድሞቻችን ለመስጠት አይከብደንም:: ፍቅር ሁልጊዜ የሚገለጸው በመስጠት ነው:: «ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?» (1ዮሐ. 3÷17-18)

ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ለእኛ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እኛም ልባችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ የክርስቶስን «የመስጠት ባሕርይ» እንቀበላለን:: ለእግዚአብሔር መስጠት ወይም መሰጠት ከእርሱ ጋር ዐብረን በተጓዝን መጠን በሕይወታችን የሚያድግ መንፈሳዊ ባሕርይ ነው::

## እኛም ሆንን ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው

ዳዊት በ1ዜና መዋዕል 29÷14 እንዲህ ብሎ ጸለየ፤ «ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና፤ ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና ይህን ያህል ችለን ልናቀርብልህ እኔ ማነኝ ሕዝቤስ ማነው?»

በዐዲስ ኪዳን ደግሞ፤ «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» (1ቆሮ. 6÷19-20፤ 1ጴጥ. 1÷18-19) ይለናል::





ኢየሱስ የሁሉ ጌታ ስለ ሆነ፣ «በእኔና የእኔ በሆነው ሁሉ ላይ ጌታ ሁን» ብለን ሁሉን ለእርሱ መስጠት ይኖርብናል:: (ሮሜ 10÷9) እግዚአብሔር እኛን «የንብረቴ ጠባቂዎች» (ባለ ዐደራዎች) ናችሁ ነው የሚለን::

ንብረት ጠባቂ (ባለ ዐደራ) የጌታውን ንብረት በጥንቃቄ የሚቈጣጠርና የሚጠብቅ ነው:: የራሱ የሆነ ንብረት የለውም::

ንብረት ጠባቂ የጌታውን ንብረት እንዴት እንደ ጠበቀ ጌታው በሚጠይቀው ጊዜ መልስ ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለበት (1ቆሮ. 4÷2)::

## የመስጠት ዐይነቶች

### ሀ. ዐሥራት

ዐሥራት ማለት የምናገኘው ሁሉ አንድ ዐሥረኛ ማለት ነው (ዘፍ. 14÷20)::

ዘሌ 27÷32፣ «ከዐሥር አንድ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሆናል::» ይላል:: ይህ ስጦታ በተለይ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ ስጦታ ነው:: የእግዚአብሔር ቤት ሥራና የእግዚአብሔር አገልግሎት መከናወን ያለበት በምንሰጠው ዐሥራት ነው:: «በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን ዐሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ» (ሚል. 3÷10):: ዐሥራትን ከመስጠት ወደኋላ ስንል እግዚአብሔርን፣ ቤተ ክርስቲያንንና፣ ራሳችንንም እንሰርቃለን:: ምክንያቱም ዐሥራትን በመስጠት የሚመጣው የእግዚአብሔር በረከት ይቀርብናል::

«ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል:: እናንተም:- የሰረቅንህ በምንድን ነው? ብላችኋል:: በዐሥራትና በበኵራት ነው::» (ሚል. 3÷8)

### ለ. መባ (በኵራት)

በኵራት ወይም መባ ከዐሥራት በላይ በተጨማሪ ለእግዚአብሔር በፈቃደኝነት የምንሰጠው ስጦታ ነው:: ይህንን ስጦታ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ለሚከናወኑ የእግዚአብሔር ሥራዎች መስጠት እንችላለን:: ከላይ የተጠቀሰው ክፍል (ሚል. 3÷8) ዐሥራትን ብቻ ሳይሆን በኵራትንም ይጨምራል::

### ሐ. የመሥዋዕትነት ስጦታ

ካለንና ከተረፈን ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተጠ ቀሰችዋ መበለት ከጐድለታችን የምንሰጠው ስጦታ ነው:: «ኢየሱስ በመዝገብ አንጻር ተቀምጦ ሕዝቡ በመዝገቡ ውስጥ ገንዘብ እንዴት እንደሚጥሉ ያይ ነበር፤ ብዙ ባለጠጎችም ብዙ ይጥሉ ነበር፤ አንዲትም ድኻ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች:: ደቀ

መዛሙርቱንም ጠርቶ፡- እውነት እላችኋለሁ፤ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድኻ መበለት አብልጣ ጣለች፤ ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና፤ ይህች ግን ከጕድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች።» (ማር. 12÷41-44)

ይህ ዐይነቱ ስጦታ የራሳችን ሳይሚላልን፣ «ጌታ ያሚላልኛል፤ እኔ የቤቱን ቀዳዳ ስሞላ እርሱ ደግሞ የእኔን ቀዳዳ ይሞላል» ብለን በእምነት የምንሰጠው ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ታማኝነቱን ያሳየናል።

ገበሬ ፍሬን አገኛለሁ ብሎ በእምነት እንደሚዘራ፣ ፍሬውንም እንደሚያጭድ፣ የመሥዋዕትነት ስጦታም እንደዚሁ ነው። የዘራነው የእምነት ዘር አፍርቶ ለራሳችን በረከት ይሆነናል (2ቆሮ. 9÷6)።

## መ. <u>ለችግረኞች መስጠት</u>

«ለድኻ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፤ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል።» (ምሳ. 19÷17)

«ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፣ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ፣ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።» (1ዮሐ. 3÷17-18)

ረዳት የሌላቸውን ልጆችና ባልቴቶችን መርዳት እንዳለብን ቃሉ ይነግረናል (ያዕ. 1÷27)።

## ሠ. <u>ለወንጌል ሥርጭት መስጠት</u>

ወንጌል በየቦታው እንዲዳረስና፣ እንዲስፋፋ የሚሰጥ ልዩ ስጦታ ነው። ለሰዎች ሁሉ ችግር ዋናው መፍትሔ ወንጌል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» ብሎ ባዘዘው መሠረት፣ የወንጌል ሥርጭት በሚደረግበት ጊዜ ለሥርጭቱ የሚሆነው አስፈላጊ ገንዘብ ጠፍቶ ወንጌል ለሰው ሁሉ ሳይዳርስ እንዳይቀር፣ በዚህ ረገድ እያንዳንዳችን ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅብናል ነው።

### <u>እንዴት እንስጥ?</u>

«ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ።» (ሉቃ. 6÷1)

«ይህንም እላለሁ፣ በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፤ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፤ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።» (2ቆሮ. 9÷6-7)





«…በፈቃዳቸው አቀረቡ። … ሕዝቡም ፈቅደው ሰጥተዋልና…፤ ደስ አላቸው።» (1ዜና. 29÷6፡9) (ክፍሉን በሙሉ ያንብቡ)

### <u>ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው ስንሰጥ፡-</u>

1. ለታይታ መሆን የለበትም።
2. ቅር እያለን ሳይሆን <u>በደስታ</u> መስጠት አለብን። እኛ በደስታ ያልሰጠነውን ስጦታ እግዚአብሔር ደስ ብሎት አይቀበለውም።
3. እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ መስጠት አለበት። ሌላ ሰው እንዳሳሰበው አይልም።
4. በሥሥት ሳይሆን በቸርነትና በልግስና መስጠት አለብን። በዘራነው መጠን እናጭዳለንና።

### <u>በመስጠት ውስጥ ያለው በረከት</u>

«ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ (የተባረከ) ነው።» (ሐዋ. 20÷35) «ስጡ፤ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፤ የተነቀነቀ፣ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በዕቅፋችሁ ይሰጣችኋል።» (ሉቃ 6÷38)

«በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን ዐሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ፣ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ስለ እናንተ ነቀዙን እገሥጻለሁ፤ የምድራችሁንም ፍሬ አያጠፋም፤ በዕርሻችሁም ያለው ወይን ፍሬውን አያረግፍም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።» (ሚል 3÷10-11)

«እግዚአብሔርን ከሀብትህ አክብር፤ ከፍሬህም ሁሉ በኵራት፣ ጎተራህም እህልን ይሞላል፤ መጥመቂያህም በወይን ጠጅ ሞልታ ትትረፈረፋለች።» (ምሳሌ 3÷9-10)

በዐጭሩ እግዚአብሔርን ከሀብትህ (ብዙም ትሁን ጥቂት) ካከበርህ፣ ትባረካለህ ማለት ነው።

በዘመናችን፣ በተለይ በምዕራቡ ዓለም አንዳንዶች እንደሚያስተምሩት፣ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ከእርሱ በረከትን ለማግኘት ሳይሆን፣ የምንሰጥበት ዋና ዐላማና ምክንያት እግዚአብሔርን ስለምንወድ ብቻ መሆን አለበት። የምንሰጠው በሰማይ መዝገብ ለመሰብሰብ እንጂ በምድር መዝገብ ለመሰብሰብ አይደለም።

«ብልና ዝገት በሚያጠፉት፣ ሌቦችም ቈፍረው በሚሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት፣ ሌቦችም ቈፍረው በማይሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና፡፡» (ማቴ. 6፥19-21)

**እግዚአብሔር የመስጠትን ምስጢር ይግለጽልን!**





## <u>ትምህርት ስምንት፡- መስጠት</u>

የመታወቂያ ቍጥር፣ ____________________

ስም፤ ____________________

አድራሻ፤ ____________________

____________________

____________________

1. የእውነተኛ መስጠት መነሻው ምንድን ነው?
2. አንድ ሰው ለእግዚአብሔር በሚሰጥበት ጊዜ ማስተዋል ያለበት ነገር ምንድን ነው?
3. የመስጠት ዐይነቶችን ከዘረዘርህ በኋላ እያንዳንዳቸው ምን እንደ ሆኑ አብራራ፡፡
4. ስጦታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው በምን ዐይነት ሁኔታ ስንሰጥ ነው?
5. መስጠት ለሰጪው ምን ይጠቅመዋል?
6. በጥናቱ ላይ በተጠቀሱት የስጦታ ዐይነቶች ምን ያህል ታማኝ ነህ? ስጦታህ ጕደለት ቢኖርበት፣ ለማስተካከል ምን ማድረግ አለብህ?